chilot.wordpress.com



፮/ በመስኩ ለኢንቨስትመንትና ለግብይቱ ዕድገትና መስፋፋት ማነቆ የሆኑ ችግሮችን በማጥናትና በመለየት መፍትሄ የመስጠት፤

፯/ በጥራትና በደረጃዎች ላይ የተመሰረተ የእንስሳት ግብይት ሥርዓት እንዲኖር የማድረግ፤

፰/ የሥጋና የቁም እንስሳት ላኪዎችን ከአምራቾችና ከግብይት ዩኒየኖችና ፌዴሬሽኖች ጋር በማስተሳሰር የእንስሳት አቅርቦት አስተማማኝ እንዲሆን የማድረግ፤

፱/ ለእንስሳት ገበያ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ-ልማቶች እንዲስፋፉ እንዲሁም ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳትና የእንስሳት ምርት የማጓጓዣ ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ፋሲሊቲዎች እንዲሟሉና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ክትትል የማድረግ፤

፲/ የእንስሳት ምርት ፍላጐትን፣ በተለያዩ የውጭ ገበያዎች ለመግባት የሚያስፈልገውን መመዘኛ እና በገበያው ውስጥ የሚገኙ ተወዳዳሪዎችን በማጥናት መረጃውን ለተጠቃሚዎች የመስጠትና የንግድ ትስስር እንዲፈጠር የማድረግ፤

፲፩/ በመስኩ ኢንቨስትመንትን የሚያስፋፉና የሚያሳድጉ፣ እንዲሁም ባለሃብቱ ዘላቂነት ያለው የእንስሳት፣ የእንስሳት ምርትና፣ የሌሎች ግብዓቶች አቅርቦት እና አገልግሎቶች እንዲያገኝ የሚያግዝ ስትራቴጂና የድርጊት መርሀ-ግብር በማዘጋጀት በመንግስት የማስወሰንና ተግባራዊነቱን የመከታተል፤

፲፪/ የኢንቨስትመንት አማራጮችንና ማበረታቻዎችን እንዲሁም የእንስሳት ምርቶችን በተቀናጀ መንገድ የማስተዋወቅ ስርአት የመዘርጋት፣ የማስጸደቅና የመተግበር፤

፲፫/ ያለውን የውጭ ገበያ ይዞ ለማቆየትና ለማስፋፋት ወደ አዳዲስ ገበያዎችም ለመግባት እንዲቻል ወቅታዊ የኤክስፖርት ስትራቴጂ የመንደፍና ተከታትሎ የማስፈፀም፤

፲፬/ በሥጋና በወተት ኢንዱስትሪ በተሻለ ደረጃ ላይ ከሚገኙ የውጭ ሀገር ተቋማት እና ተዛማጅ ዓላማ ካላቸው የሀገር ውስጥ ተቋማት ጋር የትብብር ግንኙነት የመመስረት፤

6/ provide solutions by studying and identifying bottlenecks for the development and expansion of investment and marketing in the sector;

7/ develop livestock marketing system based on quality and grades;

8/ ensure reliability of livestock supply by linking meat and livestock exporters with producers and market unions and federations;

9/ conduct follow-up on expansion of infrastructures necessary for livestock market and for the availability of facilities such as designated transportation vehicles for livestock and livestock products;

10/ provide information to users and create trade linkage by conducting assessment on the demand of livestock products, the requirement for entering foreign markets and the competitors in the market;

11/ prepare, present for approval of the government and follow-up the implementation of strategies and action plans which facilitate and develop investment in the sector and assist investors to get sustainable supply of livestock, livestock products, other inputs and services;

12/ establish, get approval and implement systems to promote investment options and incentives and livestock products in an integrated manner;

13/ develop and implement an up-to-date export strategy to maintain and boost existing export markets and to enter into new markets;

14/ establish relationships of cooperation with foreign institutions that are in better position with regard to meat and dairy industries and local institutions having similar objectives;

